# ደንብ

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

ተዛማጅ ግብአቶች፦ JEA, JEA-RC, JEA-RD, JEA-RE, JEB-RA, JEE-RA, JOA-RA
ኃላፊነት ያለው ጽ/ቤት፦ የአካዴሚ ትምህርት ዋና ኃላፊ

## የተማሪዎች ምዝገባ

### I. ዓላማ

ነዋሪ እና ነዋሪነት የሌላቸው ተማሪዎች በማለት ተለይቶ የሚወሰንበት መመሪያ የተመሠረተው በ "Montgomery County Board of Education Policy JEA" ፖሊሲ መሠረት ይሆናል፣ ነዋሪነት፣ የትምህርት ክፍያ፣ እና ምዝገባ/Residency, Tuition, and Enrollment።

ይህ መመሪያ ተማሪዎችን በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስለመቀበል/ስለመመዝገብ ህጋዊ ነዋሪዎች/bona fide residence እና ሌሎች መስፈርቶችን አሠራር ሂደትን ይወስናል

### II. ትርጉሞች

A. ህጋዊ ነዋሪነት/Bona fide residenceማለት አንድ ነዋሪ በእርግጠኝነት የሚኖርበት/የምትኖርበት እውነተኛ መኖርያ፣ እና ጊዜያዊ መኖሪያን የማያካትት ወይም በ MCPS ነፃ ትምህርት ለማግኘት በሚል ዓላማ ለአመቺነት ተብሎ የማስመሰል መኖሪያን አይመለከትም። ይሁን እንጂ፣ አሁን ባለው የመኖሪያ ቦታ ላልተወሰነ ጊዜ ወይም በቋሚነት የመኖር ዓላማ የግድ አስፈላጊ አይደለም። የተማሪ የተረጋገጠ መኖሪያ ዉሳኔ ትክክለኛ እና በእያንዳንዱን ግለሰብ ደረጃ የሚታይ መሆን አለበት።በአንፃሩ ማስረጃ ለማቅረብ ካልተቻለ፣ እንደ ህጋዊ ነዋሪ ሊጠቀስ የሚችለው የወላጅ/የሞግዚት መኖርያ ይሆናል።

የተማሪው(ዋ) ወላጆች/ሞግዚቶች ተለያይተው የሚኖሩ ከሆነ፣ በአንጻሩ መረጃ የማይገኝ ከሆነ፣ የተማሪው(ዋ) ህጋዊ መኖሪያ፣ ብቸኛው የልጅ አሳዳጊነት መብት የተሰጠው/የተሰጣት ወላጅ/ሞግዚት ወይም ልጅ/ልጅቱ በመደበኛነት-ዘወትር የሚኖርበት/የምትኖርበት እንደ ህጋዊ መኖርያ ተብሎ ይታሰባል። የተማሪው(ዋ)ን መደበኛ መኖሪያ ለመወሰን በአጠቃላይ ሁኔታዎችን ያገናዘበና በመረጃ-በተደገፈ ዝርዝር ጥናት መሆን አለበት። ሠራተኞች በተለይም በትምህርት ቀኖች ተማሪው(ዋ) የት እንደሚኖር/እንደምትኖር የተንከባካቢ/ጥበቃ ትእዛዝ ወይም ስምምነትን ጭምር ይመለከታሉ።

መመዘኛውን የሚያሟላ/የምታሟላ ብቁ ተማሪ ትክክለኛ መኖርያ የሚገለጸው ከወላጆች/ሞግዚቶች ዉጪ ራስን ችሎ/በተናጥል ሲመሰረት ነዉ።

B. ማሟላት የሚችል/የምትችል ተማሪማለት የዩ.ኤስ ዜጋ የሆነ(ች) ወይም ያልሆነ(ች) ሴፕቴምበር 1 ላይ ቢያንስ አምስት ዓመት የሞላው(ት)፣ እና የትምህርት ዓመት በሚጀመርበት ቀን ከ20 ዓመት እድሜ ያልበለጠ(ች) ማለት ነው።

C. ብቁ የሆነ(ች) ተማሪማለት የዩ.ኤስ ዜጋ የሆነ(ች) ወይም ያልሆነ(ች) ቢበዛ (18) ዓመት ዕድሜ የደረሰ(ች) ወይም ከ18 ዓመት ዕድሜ ሳይሞላ በራስ ለመመራት የተፈቀደለ(ላ)ት፣ ነገር ግን የትምህርት ዓመት በሚጀመርበት ቀን ከ20 ዓመት እድሜ የማይበልጥ/የማትበልጥ ማለት ነው።

D. የአካባቢ ትምህርት ቤት/Home school – በመኖሪያ አካባቢ ትምህርት ለመከታተል የተመቻቸ ወይም ተማሪው(ዋ) ባለበት/ባለባት ግላዊ ሁኔታ ምክንያት የግላዊ ትምህርት ፕሮግራም/Individualized Education Program (IEP) ለመከታተል የተመደበ(ች)በት ትምህርት ቤት ማለት ነው። የአካባቢ ትምህርት ቤት/home school ስለመወሰን የሚገልጽ መረጃ/ኢንፎርሜሽን በ MCPS Division of Capital Planning Office montgomeryschoolsmd.org/departments/planning ላይ ይገኛል።

## III. ያለፈ ታሪክ/BACKGROUND

ወላጆቻቸው/ሞግዚቶቻቸው በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ቋሚ መኖሪያ ያላቸው የሚያሟሉ ተማሪዎች በሙሉ ወይም (section IV.B.) ላይ በተገለጸው መሠረት ብቃት ያላቸው ተማሪዎች ከዚህ እንደሚከተለው ካልሆነ በስተቀር ተቀብሎ መመዝገብ አለባቸው:-

A. ከሌላ የትምህርት ቤት መዋቅር የታገደ(ች) ተማሪን የታገደ(ች)በት ጊዜ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እንዳይገባ/እንዳትገባ ማገድ ይችላል።

B. ተማሪው(ዋ) ተባሮ(ራ) እንደማያውቅ/እንደማታውቅ ከሪኮርድ እስከሚታይ ድረስ የተማሪ ምዝገባ ጊዜያዊ እንደሆነ ይቆጠራል።

## IV. ተማሪዎችን መመዝገቢያ ስነ ስርአት

A. ወላጆቻቸው/ሞግዚቶቻቸው በሞንትጎመሪ ካውንቲ በመደበኛነት ነዋሪዎች የሆኑ ያሚሉ ተማሪዎች በሙሉ፣ ከዚህ በታች sections IV.A.1. እና IV.A.2 ከተገለጸው ሁኔታ በስተቀር በየአካባቢያቸው ትምህርት ቤቶች ይመዘገባሉ/ይገባሉ።

1. የመኖሪያ አድራሻቸው በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የተካለሉ/MCPS consortium የመካከለኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በመምረጥ ሂደት ለመሣተፍ እና ለትምህርት ቤት ምደባ በ "MCPS Consortia office" መመዝገብ አለባቸው። ለትምህርት ቤት ምደባ የሚደረግ የምርጫ ሂደት መረጃ/ኢንፎርሜሽን በ "Division of Consortia Choice and Application Program Services" montgomeryschoolsmd.org/departments/school choice ይገኛል።

2. በዩ.ኤስ ወይም የትምህርት ሲስተም (የመከላከያ ዲፓርትመንት ትምህርት ቤቶች ወይም በውጭ አገር እውቅና የተሰጠው የአሜሪካ ኢንተርናሽናል ትምህርት ቤት) ባለፉት ሁለት ዓመታት ትምህርት ቤት ያልተከታተሉ ሴፐቴምበር 1 ላይ ዕድሜአቸው ሰባት ዓመት ወይም ከዚያ የሚበልጥ ተማሪዎች ወደ ዓለም አቀፍ የምዝገባና ምደባ "International Admissions and Enrollment (IAE)" መላክ አለባቸው። የእነዚህ ተማሪዎች ምዝገባ የሚከናወነው በ "MCPS Regulation JEA-RC"ዓለም አቀፍ እና የውጭ ተማሪዎች ምዝገባ እና ምደባ/Enrollment and Placement of International and Foreign Students መሠረት ይሆናል።

3. ከአካባቢያቸው ምድብ ትምህርት ቤት ወደሌላ ትምህርት ቤት ለመግባት የሚፈልጉ ተማሪዎችን በሙሉ ርእሰመምህር/ተወካይ ወደየራሳቸው የአካባቢ ምድብ ት/ቤት መመለስ ይኖርበ(ባ)ታል። አግባብነት ካለው ስለ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ-MCPS Regulation JEE-RA፣ስለ ተማሪ ዝውውር እና አስተዳደራዊ ምደባዎች/Student Transfers and Administrative Placements መሠረት በማድረግ ስለ ትምህርት ቤት ምደባ የመቀየር ሒደት መረጃ-ኢንፎርሜሽን መስጠት ይቻላል።

B. በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ መደበኛ መኖሪያ ያላቸው ብቁ ተማሪዎች በሙሉ ከዚህ በላይ "section IV.A." ላይ በተደነገገው መሠረት በየአካባቢ ትምህርት ቤቶቻቸው ይመዘገባሉ።

C. ተማሪዎች በአካባቢያቸው ትምህርት ቤት መመዝገብ የሚኖርባቸው ተጨማሪ ሁኔታዎች የሚያካትቱት–

1. ብቃቱ(ቷ) የተረጋገጠ ተማሪ ወላጅ/ሞግዚት ተማሪው (ዋ) ት/ቤት ከሚከታተልበት/ከምትከታተልበት አካባቢ ቤት ገዝተው ከሆነ የፀደቀበትንና ግዢው የተጠናቀቀበትን ጊዜ የሚገልጽ ኮንትራት ምዝገባ ከተደረገበት 60 ቀናት ውስጥ ወይም ት/ቤት በሚከታተልበት/በምትከታተልበት አካባቢ ከምዝገባው በ60 ቀኖች ውስጥ የሚፈጸም የስምምነት ቀኑን የሚገልጽ የኪራይ/ሊዝ ሠነድ፣ ወይም

2. ብቁ የሆነ(ች)ው ተማሪ ቤት አልባ ወይም "MCPS Regulation JEA-RD፣" ላይ እንደተገለጸው ደጋፊ የሌለው/የሌላት ወጣት የ ቤት አልባ ተማሪ ምዝገባ/Enrollment of Homeless Student፣ ወይም

3. ብቁ የሆነ(ች) ተማሪ በሞንትጎመሪ ካውንቲ በሜሪላንድ ወይም የሞንትጎመሪ ካውንቲ የማህበራዊ አገልግሎት ኤጀንሲ አማካይነት በቡድን መኖሪያ ቤት፣ በህፃናት ልጆች ማሳደጊያ፣ ይፋዊ የዘመድ እንክብካቤ ይመደባል/ትመደባለች። በዚህ ዓይነት ሁኔታ፣ MCPS Form 560-35፣ በሜሪላንድ ስቴት ቁጥጥር ወደሚደረግበት የልጆች እንክብካቤ ማስገባት እና የትምህርታዊ ሪኮርዶች ዝውውሮች /Enrollment of a Child in Maryland State-Supervised Care and Transfers of Educational Records መሞላት አለበት፣ ወይም

4. በሜሪላንድ ተቀባይነት ባለው በህጋዊነት ይፋ ያልሆነ ዘመድ በመጠጋት ነዋሪ የሆነ(ች) ብቃት ያለው/ያላት ተማሪ፦

   a) ቤተሰብ ከባድ ችግር ላይ በመውደቁ ምክንያት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ከልጁ/ከልጅቱ ጋር በጋብቻ ወይም በደም ዝምድና /fifth degree of consanguinity፣ ወደ ሚገናኙት ዘመድ በጥገኝነት ከመምጣቱ(ቷ) በፊት በሜሪላንድ ነዋሪ የሆነ(ች) ተማሪ ላይ የሜሪላንድ ይፋዊ ያልሆነ የዝምድና እንክብካቤ ተግባራዊ ይሆናል።

   b) ለተማሪው(ዋ) እንክብካቤ የሚያደርገው/የምታደርገው ዘመድ MCPS Form 334-17 መፈረም አለበ(ባ)ት በጽሑፍ የቀረበ ቃለመኃላ፦ ህጋዊ ያልተደረገ የዘመድ እንክብካቤ/AFFIDAVIT: Children in Informal Kinship Careከልጁ/ከልጅቱ ጋር ስላላቸው ዝምድና(ግንኙነት) ማረጋገጥ እና ይፋዊ/ህጋዊ ያልተደረገ የዝምድና እንክብካቤ የሚያደርጉበትን ምክንያትና ቤተሰብ ላይ ስለደረሰው ከባድ ችግር ማረጋገጫ መስጠት።

   c) በሜሪላንድ ይፋዊ ያልሆነ በዘመድ ጥገኝነት ከባድ የቤተሰብ ችግሮች ተብለው የተገለጹት፦

      (1) የህልፈተ ህይወት ሠርተፊኬት ወይም በሌላ ሠነድ/ዶኩመንት የተረጋገጠ የወላጅ/የሞግዚት መሞት፣

      (2) በሃኪም መረጃ የተረጋገጠ የወላጅ/የሞግዚት በጣም መታመም፣ የሃኪም ማስረጃ፣ ማስታወሻ፣ ወይም ሌላ ማረጋገጫ ቅጂ/ኮፒ፣

(3) ከህክምና ሰጪ አካል በደብዳቤ የተገለጸ፣ ወይም በሌላ ማረጋገጫ ወላጅ/ሞግዚት በመድሃኒት ሱሰኝነት መለከፍ፣

(4) የወላጅ/ሞግዚት እስራት፣ በህጋዊ ተቋም ሠነድ/ዶኩመንት፣ ከእስር ቤት፣ ወይም ሌላ ማረጋገጫ የተደገፈ ከሆነ፣

(5) የወላጅ/ሞግዚት ለወታደራዊ ግዳጅ የተመደቡ ከሆነ፣ በወታደራዊ ተቋም ወይም በሌላ ሠነድ ከተረጋገጠ፣ ወይም

(6) በወላጅ/በሞግዚት የተተወ፣ ህጋዊ ሞግዚትነት ያላቸው ሁሉ በሠነድነት የተረጋገጠ/notarized መግለጫ፣ ወይም የፍርድ ቤት ሠነድ፣ የማህበራዊ አገልግሎት፣ ወይም ሌላ ማረጋገጫ።

D. በሞንትጎመሪ ካውንቲ በፍርድ ቤት የተመደበ(ች) ሞግዚት ወይም ሌላ ጎልማሳ ሰው፣ ይፋዊ/ህጋዊ ካልሆነ ሰው ጋር ለመሆን ሁኔታው ያልፈቀደለ(ላ)ት፣ እና ወላጆቹ/ቿ በሞንትጎመሪ ካውንቲ መደበኛ ነዋሪነት የሌላቸው ነዋሪ የሆነ/ች እድሜው(ዋ) ከ18 ዓመት በታች የሆነ(ች) ብቁነቱ(ቷ) የተረጋገጠ ተማሪ ለመመዝገብ ከፈለገ/ች፣ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ/MCPS Regulation JEA-RE መሠረት የትምህርት ቤት ሠራተኞች IAE መጠየቅ/ማማከር ይኖርባቸዋል፣ ክፍያ ላይ የተመሠረተ ምዝገባ/Tuition Based Enrollment ክፍያው እንዲነሣ መወሰን የሚያስፈልግ ከሆነ።

E. ብቃት ያለው/ያላት ተማሪ በአካባቢ ትምህርት ቤት በቀጥታ ለመመዝገብ መስፈርቶችን ሁሉ የሚያሟላ/የምታሟላ መሆን ያለመሆኑ/ኗን ርእሰመምህር(ት)/ተወካይ እርግጠኛ ካልሆነ(ች) ርእሰመምህር(ት)/ተወካይ IAE ን ያማክራል/ታማክራለች፣ እንደአስፈላጊነቱ ወደ IAE ያስተላልፋል/ታስተላልፋለች።

F. ተማሪው(ዋ) የመመዝገቢያ መስፈርቶችን ማማሏቱ/ቷ ከተረጋገጠ፣ ርእሰመምህር/ተወካይ የሚከተሉትን የማስፈጸም ሃላፊነት አለበ(ባ)ት፦

1. የምዝገባ ሂደት ማጠናቀቅ። በምዝገባ ቀጠሮ ቀን ተመዝጋቢው(ዋ) ተማሪ መገኘት አለበ(ባ)ት፣ ተከታዩ ካልሆነ በስተቀር —

   a) በርእሰመምህር(ት)/ተወካይ የተማሪው(ዋ) መገኘት ጉዳይ ተሠርዞ ከሆነ፣ ወይም

   b) በወቅቱ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተመዘገበ(ች) እና በ MCPS ክልል ወደ ሌላ ትምህርት ቤት የሚዛወር/የምትዛወር ከሆነ።

2. በ MCPS Regulation JOA-RA ድንጋጌ መሠረት፣ ተገቢውን የተማሪ ሪኮርዶች መመሥረት።

3. በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ/MCPS Regulations JEB-RA መሠረት የተማሪ የክፍል ደረጃ እና የመማሪያ ክፍል ምደባ ምደባ፣ ወደ ክፍል መዛወር፣ ፈጣን ዝውውር፣ እና ተማሪዎች ባሉበት መቆየት እና JEA-RC፣ዓለም አቀፋዊ እና የውጭ ተማሪዎች ምዝገባ እና ምደባ።

## V. ለምዝገባ አስፈላጊ ሠነዶች

A. ከቦርድ ፖሊሲ/Board Policy ACA ጋር የሚጣጣም አድሎ የሌለበት፣ እኩልነት/ፍትኃዊ፣ እና ባህላዊ ችሎታ፣ MCPS ዜግነትን መሠረት ያደረገ አድሎ አያደርግም እና ስለ ዜግነት አቋም ማረጋገጫ መረጃ/ኢንፎርሜሽን አይፈልግም።

B. ትክክለኛ የመኖሪያ ሥፍራ የሚያመለክቱ ማስረጃዎችን የማቅረብ ኃላፊነት በወላጅ/በአሳዳጊ ወይም ብቃት ያለው/ያላት ተማሪ ላይ ነው። እንደዚህ ዓይነቶቹ ማስረጃዎች የነዋሪነት ቦታን ያመለክታሉ፣ ይሁን እንጂ፣ MCPS ተቃራኒ የሆኑ ማስረጃዎችን ካገኘ፣ ይህ ውሳኔ ሊነሳ (ሊቀለበስ) ይችላል። ከግለሰብ ማረጋገጫ በተጨማሪ፣ MCPS በክፍል-ደረጃ ወይም ትም/ቤት አቀፍ የመኖሪያ አድራሻ ማረጋገጫ የማጣራት መብት አለው።

C. በወቅቱ በ MCPS በመማር ላይ ያለ(ች) ተማሪ ቤተሰብ ወደ ሌላ የ MCPS ትምህርት ቤት አካባቢ የተዛወሩ ከሆነ፣ ወላጆች/ሞግዚቶች አዲስ ከተዛወሩበት የትምህርት ቤት አካባቢ ነዋሪ መሆናቸውን ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው።

D. በ MCPS ትምህርት ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ ተማሪን ለማስገባት/ለማስመዝገብ፣ ወይም ከ MCPS ከለቀቀ/ች በኋላ ዳግመኛ ለማስገባት/ለማስመዝገብ፣ ወላጆች/ሞግዚቶች/ብቃት ያላቸው ተማሪዎች የሚከተለው ኃላፊነት አለባቸው፦

1. MCPS Form 560-24 መሙላት፣ የአዲስ ተማሪ መረጃ/New Student Informationእና MCPS Form 565-1፣ ለድንገተኛ/አስቸኳይ ጊዜ የተማሪ መረጃ/Student Emergency Information።

2. ተማሪው(ዋ) ቤት አልባ ስለመሆኑ(ኗ) የተረጋገጠ ካልሆነ(ች) በስተቀር የሚከተሉትን ሠነዶች ማቅረብ፦

   a) የተማሪው(ዋ) ስም እና የተወለደ(ች)በት ቀን ማረጋገጫ (ተቀባይነት ያላቸው ሠነዶች የልደት ሠርተፊኬት፣ ፓስፖርት/ቪዛ፣ የኃኪም ሠርተፊኬት፣ የጥምቀት ወይም የቤተክርስቲያን ሠርተፊኬት፣ የሆስፒታል ሠርተፊኬት፣ የወላጆች ኖተሪ የተረጋገጠ ቃለመኃላ፣ የልደት ቀን ምዝገባ፣ ሌላ ህጋዊ ወይም በኖተሪ የተረጋገጠ መታወቂያ)

   b) ፎተግራፍ ያለበት የወላጅ/ሞግዚት መታወቂያ ማረጋገጫ (ተቀባይነት ያላቸው ሠነዶች የመንጃ ፈቃድ፣ ፓስፖርት፣ ከተሽከርካሪዎች አስተዳደር (MVA) መታወቂያ ካርድ ወይም ሌላ ህጋዊነት ያለው መታወቂያ)

   c) ወላጅ/ሞግዚት ከተማሪ(ዋ) ጋር ያላቸው ግንኙነት ወይም የተማሪው(ዋ)ን አሳዳጊነት (ተቀባይነት ያላቸው ሠነዶች ወላጆችን የሚገልጽ የልደት ሠርተፊኬት፣ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ፣ ለመለያየት የተደረገ ስምምነት፣ ወይም የፍቺ መረጃ ወይም ሌላ ህጋዊነት ያለው መለያ)

   d) የክትባት ማረጋገጫ

      (1) ተቀባይነት ያላቸው ሠነዶች የሜሪላንድ የጤና ዲፓርትመንት ቅጽ 896/Maryland Department of Health (MDH) Form 896 የሜሪላንድ የጤና ዲፓርትመንት የክትባት ሠርተፊኬት/Maryland Department of Health Immunization Certificate፣ወይም ከሃኪም ወይም ከጤና ክሊኒክ በኮምፒውተር የተጻፈ ቅጽ

(2) ወላጆች/ሞግዚቶች ክትባት(ቶች) በኃይማኖታዊ እምነታቸው ምክንያት የማይፈልጉ ከሆነ ቅጽ/MDH Form 896 ተገቢ ሠነድ ይሆናል

e) የነዋሪነት ማስረጃ

(1) የቤት ባለቤትነት (ተቀባይነት የሚኖረው ወቅታዊ የንብረት ታክስ ቢል ነው)

(2) ተከራይ

(a) ተቀባይነት የሚኖረው ወቅታዊ የኪራይ/የሊዝ ሠነድ ነው።

(b) የመጀመሪያው የኪራይ/ሊዝ ሠነድ ወቅቱ ያለፈበት ከሆነ፣ ወቅታዊ የዩቲሊቲ ክፍያ ቢል ወይም የኪራይ/ሊዝ የተራዘመበት ሠነድ መቅረብ አለበት

(3) የጋራ/የደባልነት ቤት

ወላጅ/ሞግዚት/ብቁ ተማሪ በ MCPS ትምህርት ቤት አካባቢ በህጋዊነት ከሚኖሩ የቤት ባለቤት ወይም ከተከራይ ጋር ተጋርተው በደባልነት እየኖሩ ትምህርት ቤት ለማስመዝገብ ከፈለጉ ቅጽ - MCPS Form 335-74፣ የቤት ደባልነት መግለጫ/Shared Housing Disclosure፣ መሞላት አለበት።

(a) በ "section V.D.2.e)(1) ወይም (2) ላይ ባለው መግለጫ መሠረት ወላጅ/ሞግዚት ከሚኖሩበት የቤቱ ባለቤት ወይም ተከራይ MCPS Form 335-74 ተሞልቶ የኗሪነት ማረጋገጫ እንዲቀርብ ያስፈልጋል፣ እና

(b) ወላጅ/ሞግዚት/ብቁነት ያለው(ያላት) ተማሪ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ትምህርት ቤት ለመከታተል ብቻ ሳይሆን መደበኛ መኖሪያቸው ከእነርሱ ጋር መሆኑን በማረጋገጥ የቃለመኃላ ቅጽ "MCPS Form 335-74" ሞልተውና ፈርመውበት ኖቶራይዝ ተደርጎ መቅረብ አለበት፣ እና

(c) ወላጅ/ሞግዚት/ብቁነት ያለው(ያላት) ተማሪ በዚህ አድራሻ ነዋሪዎች ስለመሆናቸው ማረጋገጫ ሦስት ዶኩመንቶች ማቅረብ አለባቸው። (እነዚህ ዶኩሜንቶች ለምሳሌ፡- በ MCPS ..በ "Student Record Keeper Manual""MCPS Form 560-24B" "Quick Guide to Enrollment" ውስጥ ተካተዋል። ተሞልቶ የተፈረመበትና ኖሮራይዝ የተደረገ የ "MCPS Form 335-74" ቅጽ ከሦስቱ እንደ አንድ የመኖሪያ አድራሻ ማረጋገጫ ሊቆጠር ይችላል።)

(4) "MCPS Form 560-34" በመጠቀም፣ የትምህርት ቤት ሠራተኛ ወይም የተማሪዎች ሠራተኛ የቤት ጉብኝት "Documentation of Residency Through Home Visit"፣ ወላጆች/ሞግዚቶች/ብቁነት ያለው(ያላት) ተማሪ አስፈላጊ ዶኩሜንቶችን ለማቅረብ በማይችሉበት ወቅት ለነዋሪነት ማረጋገጫነት ለመጠቀም ይችሉ ይሆናል።

## VI. ይግባኝ የመጠየቂያ ሥርአት/ሂደት

በቦርድ ፖሊሲ/Board Policy JEA መሠረት፣ ነዋሪነት፣ የትምህርት ክፍያ፣ እና ምዝገባ/"Residency, Tuition, and Enrollment"፣ እውነተኛ/ያልተጭበረበረ ነዋሪነትን በሚመለከት ከርእሰ መምህር(ት) ስለተሰጠ ውሳኔ ይግባኝ መደረግ ያለበት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ/"MCPS Regulation KLA-RA" ስርዓት ተከትሎ መሆን አለበት ለማህበረሰብ ጥያቄዎች እና ቅሬታዎችን ምላሽ መስጠት/Responding to Inquiries and Complaints from the Public።

ስለ ነዋሪነት እና ስለ ቀውስ በሚቀርቡ ይግባኞች ላይ የሚከተሉት ቅደምተከተሎች መታየት አለባቸው፦

A. የይግባኝ ሂደትን ለማስኬድና በፍጥነት ውሳኔ ለማሰጠት "IAE" ድጋፍ ያደርጋል፣ በተለይም ትምህርት ቤት ተጀምሮ ከሆነ እና ክፍል ለመከታተል ተማሪው(ዋ) እየተጠባበቀ(ች) ከሆነ።

B. ወላጅ(ጆች)/ሞግዚት(ቶች) ይግባኝ እየተካሄደ ባለበት ወቅት ተማሪው(ዋ) የክፍል ትምህርት እንዲከታተል/እንድትከታተል የሚፈልጉ ከሆነ፣ በ "MCPS Regulation JEA-RE" ላይ እንደተገለጸው ከአመት የትምህርት ክፍያ 10 ፐርሰንት እንዲከፍሉ ይጠበቅባቸው ይሆናል፣ ክፍያን መሠረት ያደረገ ምዝገባ/"Tuition Based Enrollment""MCPS Form 335-73A"ነዋሪ ያለሆነ(ች)፣ ለትምህርት ከፋይ ተማሪ ምዝገባ ጥያቄ/"Request to Enroll Nonresident, Tuition-Paying Student"መሞላት አለበት። የመጀመሪያው ውሳኔ ከተለወጠ ወይም ከተሻሻለ የትምህርት ክፍያው/Tuition በሙሉ ወይም በከፊል ተመላሽ ይደረጋል።

**ተዛማጅ ምንጮች/Related Sources፦** Annotated Code of Maryland, Education Article, §7-301, §7-305, and §7-403; Code of Maryland Regulations, §13A.02.06.02, Definitions, §13A.02.06.03, State Financial Assistance under the Foundation Program, §10.06.04.03, Required immunizations, §10.06.04.05, Religious exemptions; MCPS Student Record Keeper Manual.

**ስለ ደንቡ ታሪክ/Regulation History፦** ቀደም ሲል የ Regulation 355-3 እና JEB-RA አካል የነበረ ሲሆን፣ እንደ አዲስ የተለየ ደንብ ሆኖ የተመሠረተው ኦገስት 26/1987 ነው፣ ሜይ 2/1995 ተሻሽሏል፣ ኦክቶበር 4/1996 ተሻሽሏል፣ ጁን 27/1997 ተሻሽሏል፣ ጁላይ 6/2001 ተሻሽሏል፣ ማርች 10/2005 ተሻሽሏል፣ ፌብሩወሪ 6/2008 ተጨማሪ ግብአት ተደርጎበታል፣ ጁላይ 29/2015 ክለሳ ተደርጓል፣ ሴፕቴምበር 24/2018 ክለሳ ተደርጓል፣ ኦክቶበር 10/2019 ተጨማሪ ግብአት ተደርጓል።